በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 11


**መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ**

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ግንቦት ፳ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

**መቀራረብ**

- በሰው ልጆች መካከል ከሚገኙ ግኑኝነቶች ሁሉ በጋብቻ የሚታየው መቀራረብ እጅግ የላቀ ነው፡፡ በጋብቻ የሚታየው መቀራረብ ከእግዚአብሔር ጋር ከሚኖረን ግኑኝነት ቀጥሎ የሚገኝ የላቀ ግኑኝነት ሆኖ ሊቆጠር ይችላል፡፡
- ጌታችን አምላካችንም በዚህ ብቸኛ በሆነው ግኑኝነት ስላለው መቀራረብ ሲናገር ‹‹እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ፦ ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥አለም፡፡ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው፡፡›› *ማቴ 19፡4-6፡፡* ብሏል፡፡
- ጌታችን በቃሉ ጋብቻ ባልና ሚስትን አዳምና ሔዋን ከውድቀት በፊት በገነት ወደነበሩበት የከበረ ሕይወት የሚመልስ እውነታ መሆኑን በዘፍጥረት ለአዳምና ለሔዋን በጋብቻ ሊሰጣቸው ቃል የገባላቸውን የደስታና የአንድነት ስጦታ በመጥቀስ ተናግሯል፡፡
- ይህም በምስጢረ ተክሊል አማካኝነት ባልና ሚስት በክርስቶስ እርስ በርሳቸው እንዲሁም ከክርስቶስ ጋር አንድ የሚሆኑበትን ብሎም ኃጢአት ወደዓለም ሳይገባ ወደ ነበሩበት ሕይወት በምስጢሩ አማካይነት እንደሚሸጋገሩ መገለጹ ታላቅ ምልክት ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

**መቀራረብ**

- ቅዱስ ጳውሎስም በባልና ሚስት መካከል ያለውን መቀራረብ ወይም አንድነት በክርስቶስና በቤተ ክርስቲተተን መካከል ካለው አንድነት ጋር መስሎ ጽፏል። በመልእክቱም ባሎች ስለሚስቶቻቸው ነፍሳቸውን ለመስጠት ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ አሳስቧል። ‹‹ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።›› ***ቀዳ ቆሮ 7፡3።***
- ቤተ ክርስቲያን ለመድኃኒትዋ ታዛዥና የመድኃኒትዋም ወዳጅ እንደሆነች ሚስቶችም ባሎቻቸውን እንዲወዱና ለባሎቻቸውም ራሳቸውን እንዲሰጡ ‹‹ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ።›› ***ኤፌ 5፡22።*** በማለት አስታውሷቸዋል።

**በክርስቲያናዊ ጋብቻ ውስጥ የሚገኘው መቀራረብ በሚከተሉት ሦስት መንገዶች ራሱን በተግባር ይገልጣል።**

1. **በችሎታ መቀራረብ**

- በርካታ ጥንዶች የሰው ልጆች ተራ ከሆነው ውጫዊ ውበት ይልቅ በአመለካከታቸው የሚሳሳቡ የመሆናቸውን እውነታ በመዘንጋት ጋብቻን አካላዊ መቀራረብ ብቻ እንደሆነ አድርገው ይቆጡሩታል።
- ስለዚህ ባለትዳሮች ደስተኛና በእርካታም የተሞሉ መሆን ይችሉ ዘንድ ብቃት ባለው ችሎታቸው በሚያቀራሩቡአቸው አቅጣጫዎች ላይ ጠንክረው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

**መቀራረብ**

1. **በችሎታ መቀራረብ…**

- ምናልባት መጽሐፍ አንብበው በመጽሐፉ ላይ ለመወያየት ወይም ፊልም አይተው በፊልሙ ላይ ለመነጋገር ሊፈልጉ ይችላሉ፣ እንዲሁም በመካከላቸው ለሚኖር ጤናማ መግባባት በሚረዳ የጋራ ፍላጎትና መግባባቱንም ለማምጣት ስለሚሠሯቸው የጋራ ሥራዎች ሊያጠኑ ይችላሉ፣ በተጨማሪም አንዳቸው የሰሙትን የስብከት ካሴት ወይም ያነበቡትን መንፈሳዊ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ለሌላው መስጠትም ለመቀራረቡ ማደግ የሚመከር አቅጣጫ ነው፣ እንዲህ ያሉ ድርጊቶች በችሎታ ለማቀራረብ ከመርዳቱም በላይ መቀራረባችንም ያደገ እንዲሆን ይረዳዋል፡፡
- ባለትዳሮች የበለጠ ለመቀራረብ በሚያስችላቸው ሁኔታ ላይ ዘወትር ተጋግዘው መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳንድ የሚወዱትንና የሚጠሉትንም ነገር በተመለከተ ስላላቸው መነሳሳት አውጥተው መነጋገርም ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ባለትዳሮች ልጆቻቸውንም የሚያሳድጉበትን ስልታዊ መንገድም ማዘጋጀትና በየጊዜው ስልታዊ አካሄዳቸውንም መገምገም፣ ስልታዊ አካሄዳቸውንም ለመለወጥ ወይም ለማሻሻልና የተለያየ የሆነ ሐሳባቸውንም ለመቀባበል ፈቃደኞች መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

**መቀራረብ**

2. በስሜት መቀራረብ

- ስሜታዊ መቀራረብ ተጋቢዎች ጋብቻን በመሠረቱበት የመጀመሪያዎቹ ወራት ሕይወታቸውን የሚጀምሩበት ነው፡፡ ይህም መቀራረብ የመጀመሪያ ልጃቸውን ሲያገኙ ሊዘበራረቅና ውጥረት ያለበት ሕይወት ተጋቢዎቹን ወደተለያየ አቅጣጫ ሲመራቸው የመደብዘዝ አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል፤ ይህ ልጆችንም እስከመጉዳት ይደርሳል፡፡
- ይሁን እንጂ በክርስቶስ ለሆነ ማንኛውም ጋብቻ ስኬት ይህን ስሜታዊ መቀራረብ ጠብቆ ለማሳደግ ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡
- በባልና በሚስት መካከል ያለው ግኑኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረንን ግኑንነት ይመስላል፡፡ *ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግኑኝነት ቅዝቃዜ የገጠመው፣ ጸሎታችን ትጋት የጎደለው፣ ጾማችንም በልማድ ብቻ የምናደርገው፣ አገልግሎታችንም አንዳንድ ጊዜ እንደሚታየው በተከፈለ ልብ (ሙሉ ባልሆነ ልብ) የሚቀርብ ሊሆን ይችላል፡፡*
- እንደዚሁ የባልና ሚስትም ግኑኝነት ፍጹም መልካም ስሜት የማይነበብበት፣ አንዱ በአንዱ ነገር የማይገባና በአንድ ጣራ ሥር የሚኖሩ ብቻ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ፡፡
- ነገር ግን ይህ ምልክት የሚጠበቅ ስለሆነ እንደ ትልቅ አደጋ ወይም ግኑንነቱ እንዳበቃለት ሆኖ መቆጠር የለበትም፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 11

**መቀራረብ**

2. በስሜት መቀራረብ...

- እንዲህ ያለ ነገር ሲፈጠር በማስተዋል ማሰብ የሚኖርብን ወደዚህ ወደደከመ የስሜት ባትሪ ስሜትና ኃይልን መልሰን መሙላት ስለሚያስችለን ስልትና ይህንም በተግባር ስለምንፈጽምበት መንገድ ነው፡፡
- ይህንም ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ አማራጮች ቢኖሩም የመጀመሪያው ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን በጥረታችን ሁሉ ይረዳን ዘንድ መጠየቅ ነው፡፡
- ሁለታችሁም ግኑኝነታችሁ እንደቀዘቀዘ ስትረዱ ጌታችን ስሜታችሁን ወደ ሚበልጠው መልካም ደረጃ የምትመልሱበትን መንገድ ይመራችሁ ዘንድ በአንድነት ሆናችሁ በመጸለይ መጀመር ታላቅ ብልህነት ነው፡፡
- ከሁለት አንዳችሁ ክህደት እንደተፈጸመ ስታምኑ ሌላው ካልተቀበለው ስለሆነው ሁሉ ባይስማማም/ባትስማማም በጉዳዩ ላይ ይጸልይ/ትጸልይ ዘንድ ዕድል ሰጥታችሁ አብራችሁ ለጸሎት ተግታችሁ ቁሙ፡፡
- ሌላው ስሜታችሁን የምትቀሰቅሱበትና ወደ ነበረበት መቀራረብ የምትመልሱበት መንገድ ሁለታችሁ ብቻ ተያይዛችሁ ወጣ ወዳለ ሥፍራ ሄዳችሁ ጊዜ በመውሰድ ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

**መቀራረብ**

2. **በስሜት መቀራረብ…**

- ከተለመደው ሥፍራ ወጣ ብለን በተለየ ሥፍራ እረፍት መውሰዳችን በሕይወታችን ጤናማ ለውጦችን ለማምጣት ይረዳናል፡፡
- በዚህም ጊዜ አስቀድሞ አብራችሁ በመሆን ጥሩ ጊዜ ያሳለፋችሁበትን ቦታ መምረጥም የተሻለ ነው፡፡ ለምሳሌ የጫጉላ ጊዜያችሁን ያሳለፋችሁበትን ወይም ጥሩ ማስታወሻ ያለውን ቦታ ተጠቀሙ፡፡
- ወንዶች ብዙ ጊዜ ተግባራዊ የሆነው የሕይወት ድርሻ ላይ ባላቸው ተሳትፎ ስለሚወጠሩ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ሴቶች ወስደው ኃላፊነቱን ቢወጡ መልካም ነው፡፡ ስለዚህ የተወደዳችሁ ሴቶች ልጆቻችን! ተያይዛችሁ ወጣ ወዳለ ሥፍራ ለመሄድ የሚያስችለውን መርሐ ግብር ንደፉ፡፡ ታዲያ የባሎቻችሁን መርሐ ግብር ማዕከል ያደረገ ይሁን፡፡

3. **በአካል መቀራረብ…**

- አንዳንዶች ይኸኛው ነጥብ በመጨረሻ ያስቀመጥኩት ከሁሉ ያነሰ ስለሆነ ሊመስላቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ እውነት አይደለም!
- በክርስቶስ ለሆነ ጋብቻ ስኬታማነት አካላዊ መቀራረብም ከፍ ያለ አስተዋጽዖ አለው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

## መቀራረብ

**3.** በአካል መቀራረብ…

- ጌታችንም ወንድ ና ሴትን በጋብቻ ‹‹እግዚአብሔር አንድ አደረጋቸው›› ‹‹አንድ ናቸው እንጂ ከእንግዲህ ሁለት አይደሉም… በሥጋም በመንፈስም አንድ ናቸው … እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየው፡፡›› በማለት ደጋግሞ ነግሮናል፡፡
- ባልና ሚስት ‹‹አንድ አካልና አንድ መንፈስ›› በሆኑበት በተቀደሰው አካላዊ መቀራረብ ደስ ይላቸው ዘንድ የጌታችን ቅዱስ ፈቃዱ ነው፡፡ ይህም መንገድ ከትዳር አጋራችን ጋር ያለንን አካላዊ መቀራረብ ልንመለከት የሚገባበት አቅጣጫ ነው፡፡
- ይህ አካላዊ መቀራረብ ከላይ የተመለከትናቸውን ነጥቦች ጨምሮ በባልና ሚስት መካከል መተዋወቅን (ፈቃደ ሥጋን መፈጸምን - የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ማድረግን) ይመለከታል፡፡
- በትዳር በአካል መተዋወቅ (የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ማድረግ) ዝቅ ያለ ግምት ተሰጥቶት፣ ወይም ከልክ በላይ ተጋኖ፣ ወይም የተሳሳተ ግምት ተሰጥቶት መመልከት እንደ አሳዛኝ ነገር የሚቆጠር ነው፡፡
- በመጀመሪያው ግምት በኩል የግብረ ሥጋ ግኑኝነት እንደ ተጨማሪ ነገር ስለሚቆጠር ምንም ዓይነት ጥንቃቄ አይደረግለትም ትኩረትም አይሰጠውም፣ ይህም በርካታ ፈተናዎችን የሚያስከትል የተሳሳተ አመለካከት ነው፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

## መቀራረብ

3. በአካል መቀራረብ…

- በሌላ በኩል የጋብቻ ዋነኛው ዓላማ የግብረ ሥጋ ግኑኝነትን ማድረግ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ይህም በተጋቢዎች ትዳር ላይ ከፍተኛ አደጋ ያስከትላል፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ በጋብቻ ውስጥ የሚኖረውን የግብረ ሥጋ ግኑንነት ቅድስና አስመልክቶ ‹‹መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፡፡›› *ዕብ 13፡4፡፡* ብሎናል፡፡
- ስለ ግብረ ሥጋ ግኑኝነት የሚታየው የተሳሳተ አመለካከት የመነጨው የሥጋ ፈቃድን በሕገ ወጥ መንገድ መፈጸምን (ዝሙትን) አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ ከሰጠን ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ግኑኝነት በባለትዳሮች መፈጸሙ ንጹሕ እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡
- እግዚአብሔር ሌላውን ነገር ሰው ደስ እንዲሰኝበትና እንዲረካበት እንደ ፈጠረ ሁሉ የግብረ ሥጋ ግኑኝነትን ለሰው ልጆች ደስታ እንዲሆን ፈጥሮታል፡፡
- እግዚአብሔር ‹‹እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው፡፡›› *ዘፍጥ 1፡28* ብሎ በፈቀደ ጊዜ ለአዳምና ለሔዋን በገነት ሳሉ ይህን ጸጋ መስጠቱ ግልጽ ሆኖአል፡፡ በተጨማሪም ይህኑ የመሰለውን ሐሳብ ተደግሞ ‹‹ከጕብዝናህም ሚስት ጋር ደስ ይበልህ፡፡›› *ምሳ 5፡18፡፡*

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

**መቀራረብ**

3. **በአካል መቀራረብ…**

- በክርስቲያናዊ ትዳር የግብረ ሥጋ ግኑኝነትን አስመልክቶ የተሰጠው እጅግ ግልጽና ልዩ ምክር ደግሞ ‹‹ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት።ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለ መግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።›› *ቀዳ ቆሮ 7፡2-5።* የሚለው ነው።

4. **መንፈሳዊ መቀራረብ**

- የሰው ልጆች ሁሉ ለራሳቸውም ሆነ ለሚወዱት ሁሉ ደስታን እንዲሆን ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን በውስጣቸው ያለውን መንፈሳዊ ባዶነት እስካልሞሉ ድረስ ወደ ፍጹም ደስታ ግን ሊደርሱ አይችሉም።
- ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት በማድረግ ደስ እስካልተሰኘን ድረስ ባዶ ነን።
- ብቸኛው እውነተኛ ደስታ ያለው ክርስቲያናዊ ትዳር በክርስቶስ ቁጥጥር ሥር ያለ ትዳር ነው።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ... - ክፍል 11

## መቀራረብ

4. መንፈሳዊ መቀራረብ...

- መንፈሳዊ መቀራረብ የሚፈጠረው ተጋቢዎቹ የሕይወታቸውን ማሽከርከሪያ ይመራ ዘንድ ለጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃደኛነት ስንሰጥ ነው።
- ክርስቶስ የተጋቢዎቹን ሕይወት ሲቆጣጠር ባልና ሚስቱ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ሐሳብ ማሰብና ደስ የሚያሰኘውን ሥራ ለመሥራት ይጀምራሉ፣ ይቀጥሉበታልም። የዚህም ሕይወት ውጤቱ የበዛ ፍቅርን፣ ደስታንና ባለትዳሮች ሁሉ የሚሹትን የማይነዋወጽ ሰላም ማግኘት ነው።
- ባለትዳሮቹ አብረው የሚጸልዩ፣ መጽሐፍ ቅዱስን፣ ትርጓሜያቱንና ሌሎችንም መንፈሳውያን መጻሕፍት የሚያነብቡ፣ አብረው የሚያገለግሉ፣ ወደ ቅዳሴ አብረው ለማስቀደስ የሚገሰግሡና የጌታችንንም አማናዊ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደም በየጊዜው አብረው የሚቀበሉ ከሆኑ ይህ መንፈሳዊ መቀራረባቸው ጸንቶ ይኖራል።

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

## መንፈሳዊ ቅንዓት

- አምላካችን እኛን ለማዳን መቅናቱ ከዙፋኑ ወርዶ ሊያድነን እንዲመጣ፣ ሥጋችንን እንዲለብስ፣ ባለጠጋ ሲሆን በድህነት እንዲመላለስ፣ እንዲሰደብና እንዲከሰስ በመጨረሻ ዘላለማዊ ሕይወትንና ትንሣኤንም ሊሰጠን በመስቀል ለመሞት አብቅቶታል፡፡
- መንፈሳዊ ቅንዓት ያለው ባል ለሚወዳት ሚስቱ ፍቅሩን የማሳየት ብቃት ያገኛል፡፡ በጋብቻቸው ዕለት ቃል ሲገባ እንደተናገረው ‹‹እርስዋን ደስ የሚያሰኛትንም›› ለማድረግ ዘወትር ይፋጠናል፡፡  የምትፈልገውንም እንደ አቅሙ ለማድረግ ምንም ዓይነት ቸልተኝነት አያሳይም፡፡ በችግርዋና በሕመምዋ ጊዜ ሁሉ፣ በነፍሰጡርነትዋም ሆነ በምትወልድበትም በምጥ ጊዜዋም ሁሉ ይረዳታል ያግዛታል፡፡
- በርካታ ባሎች ሚስቶቻቸው ሲወልዱ ገብተው አብረው የመሆን ዕድል እየተሰጣቸው ነው፡፡
- መንፈሳዊ ቀናነት (ቅንዓት) ያላት ሚስት ባልዋን የሚያስደስተውንና የሚያረካውን ሁሉ ለማድረግ የተቻላትን ያህል ትጣጣራለች፡፡
- የባልዋ ስኬት ዘወትር ደስ ያሰኛታል፤ በርሱም ሆነ በሚሠራው በጎ ነገር ሁሉ የሚሰማትን ኩራት ከመግለጽም አትቆጠብም፡፡

# የክርስቲያናዊ ትዳር ሀ ሁ… - ክፍል 11

## መንፈሳዊ ቅንዓት

- በችግሩ ጊዜ ሁሉ ልትረዳው ዘወትር የተዘጋጀችና በአገልግሎትም ሆነ በማንኛውም ሥራ የጸና እንዲሆን ታበረታታዋለች፡፡
- መንፈሳዊ ቅንዓት ያላቸው ባልና ሚስት ግኑኙነታቸውን በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለማሳደግ (ለማሳመር)፣ ወደርሱም የበለጠ ለመቅረብ፣ እርሱን ለማገልገል፣ ቤታቸውንም እርሱ የሚኖርባትና የሚያስተዳድርባት ‹‹ቤተ ክርስቲያን›› ለማድረግ የተሰናዱ ናቸው፡፡
- ‹‹እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድር ነው?›› *መዝ 17፡16፡፡*
- ‹‹የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፡፡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን፡፡›› *ኢያ 24፡15፡፡*

# ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org